ቁጥር/Ref.No/TI/111 /CWD/2018
Date/ቀን/:- ታህሳስ 03 /2018 ዓ.ም.

የአካባቢ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

ኩባንያችን ጢስ እሳት ዉኃ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር በም/ጎጃም ዞን በማቻከል ወረዳ እየተገነባ ለሚገኘው የተምጫ አነስተኛ ደረጃ መስኖ ፕሮጀክት (Lot 1&2) እና በማዕ/ ጎንደር ዞን በምስ/ በለሳ ወረዳ እየተገነባ ለሚገኘው የአዞ ባህር መስኖ ፕሮጀክት (Lot 1&2) ከተለያዩ ተቋማት ጋር ውል በመውሰድ የግንባታ ስራዎችን እያከናወነ ሲሆን ውል ከወሰደባቸው የስራ ዝርዝር ውስጥ የጉልበት ስራ በዘርፉ ከተሰማሩ ደረጃ - 4 እና ከዚያ በላይ WC ወይም GC በሆኑ እና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ከሚችሉ ንዑስ ተቋራጮች መካከል አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል፡፡

1. ንዑስ ተጫራቾች ለ 2018 ዓ.ም የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ፣ የንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ የምሰክር ወረቀት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ሰርተፊኬት እንዲሁም የታክስ ክሊራንስ ማስረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ንዑስ ተጫራቾች የመስሪያ ዋጋቸውን ሲሞሉ ለስራው የሚያስፈልግ ማንኛውም የሰው ሀይል ወጪን ያካተተ እንደሆነ ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ንዑስ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በባህር ዳር ከተማ፣ አጼ ቲወድሮስ ክፍለ ክተማ፣ ማራኪ ቀበሌ፣ ቴዲ የአሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋም ፊት ለፊት ከሚገኘው የኩባንያው ዋና መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 010 /የኮንትራት አስተዳደርና ገበያ ልማት መምሪያ/ በነጻ (ያለ ክፍያ) መዉሰድ ይችላሉ፡፡
4. ጨረታው ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ታህሳስ 03 /2018 ዓ.ም. ጀምሮና ቅዳሜን ጨምሮ ለ07 ተከታታይ የስራ ቀናት ብቻ አየር ላይ የሚቆይ ሲሆን በ7ኛው ቀን ከቀኑ 9:00 ሰዓት ጨረታው ተዘግቶ በዚሁ ቀን ከቀኑ 9:30 ሰዓት ባህር ዳር ከተማ፣ አጼ ቲወድሮስ ክፍለ ክተማ፣ ማራኪ ቀበሌ፣ ቴዲ የአሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ ተቋም ፊት ለፊት በሚገኘው የኩባንያው ዋና መ/ቤት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች በተገኙበት ይከፈታል፡፡
5. የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ጨረታው በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ተዘግቶ ይከፈታል፡፡
6. ስለጨረታው በጽሁፍም ሆነ በስልክ ማብራሪያ /Clarification/ መጠየቅ ይቻላል፡፡

TIS ISAT WATER WORKS PLC

Scanned by CamScanner

7. ንዑስ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ 1% ተቀባይነት ያለው የጨረታ ማስከበርያ ዋስትና (Bid Bond) በባንክ የተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ (CPO)፣ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
8. ተጫራቾች በጨረታ መወዳደሪያ ሰነዱ /Bid document/ መሰረት የቴክኒካል ሰነዳቸውን፣ ዋጋ ማቅረቢያቸዉን እና የጨረታ ማስከበሪያቸዉን በታሸገ ፖስታ እና የድርጂቱን ስም በማስቀመጥና ማህተም በመምታት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
9. ንዑስ ተጫራች ድርጅቶች በሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ ላይ ለእያንዳንዱ ስራ ነጠላ ዋጋ እና ጠቅላላ ዋጋውን በማያሻማ ሁኔታ በትክክል በእጅ ጽሁፍ መሙላት አለባቸው።
10. በሚቀርበው የቴክኒካልና የመስሪያ ዋጋ ማቅረቢያ ሰነዶች ላይ የድርጅቱ ሕጋዊ ተወካይ ፊርማና የድርጅቱ ማህተም ሊይኖርበት ይገባል።
11. ንዑስ ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመስሪያ ዋጋ የግንባታ እቃዎችን ከዋናው ተቋራጭ መጋዘን ተሸከርካሪ ላይ መጫንም ሆነ ማውረድ ስራ፣ በሰው ሀይል ማጓጓዝ፣ መገንቢያ፣ የገርጋታና የሌሎች ወጭዎችን የሚሸፍን ይሆናል። ሌሎች ከስራዎች ጋር የተያያዙ የጉልበት ወጪዎች በተሰጠው ዋጋ ላይ ተጠቃለው መቅረብ ይኖርባቸዋል።
12. የጨረታዉ አሸናፊ አሸናፊነቱ በጽሁፍ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 5 ቀናት ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ የጠቅላላ መስሪያ ዋጋዉን 10% በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ወይም 30% በኢንሹራንስ የተዘጋጀ ዋስትና የዉል ማስከበሪያ በማቅረብ ዉል የመያዝ ግዴታ ይኖርበታል።
13. ለሁለቱም ፕሮጀክቶች ለእያንዳንዳቸው ስራውን ሰርቶ የማጠናቀቂያ ጊዜ የግንባታ ቦታ ርክክብ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ 06 ወር ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት።
14. የጨረታዉ ውድድር አሸናፊ የሚለየው በፕሮጀክት ሳይሆን በሎት(Lot) ነው።
15. ንዑስ ተጫራቾች በጨረታ ወቅት የሚያቀርቡት ዋጋ ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ውል እስከሚያዝበት ቀን ቢያንስ ለ30 ቀናት ፀንቶ መቆየት የሚችል መሆን አለበት።
16. ሥራውን በገባው ውል መሠረት ያላከናወነ ንዑስ ተቋራጭ ለእያንዳንዱ የዘገየበት የግንባታ ቀናት የውሉን ጠቅላላ ዋጋ 0.1% በየቀኑ በቅጣት መልክ ይከፍላል። ነገር ግን የጉዳት ካሳ ቅጣቱ ከ10% በላይ መብለጥ የለበትም።
17. ይህ የአካባቢ ግሸር ግልፅ ጨረታ የውል አካል ሆኖ ይወሰዳል።
18. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ንዑስ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል አይችሉም።

TIS ISAT WATER WORKS PLC

Scanned by CamScanner

19. ጨረታው ሲከፈት የጨረታውን ሂደት ለማዛባት የሚሞክሩ ንዑስ ተጫራቾች ከጨረታው ውጭ ይሆናሉ። ለወደፊቱም ድርጅቱ በሚያደርጋቸው ሌሎች ጨረታዎች ላይ አይሳተፉም። ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናም ይወረሳል።
20. ኩባንያው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው። ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥራችን 058-220-48-26/ በፋክስ ቁጥራችን 058-220-48-30 መጠየቅ ይችላሉ።

ኩባንያው

Scanned by CamScanner